# መልክዐ አበዊነ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ (ዘአኀተሞ ገብረ ሥላሴ)

## መልክዐ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ-ግዕዝ

፩. ለዝክረ ስምክሙ ሰላም ለዝክረ ስምክሙ ወለሥዕርትክሙ በፍቅድ ለርእስክሙ ጽሁድ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ዘቤተ አእምሮ አዕማድ፤ ቀስሙ ማሕሌትየ በልሳንክሙ ንዑድ፤ እስመ ጊዜ ማዕረር አልጸቀ ወበጽሐ ገሚድ፡፡

፪. ለቀራንብቲክሙ ወለአዕይንቲክሙ ሰላም ለቀራንብቲክሙ ወለአዕይንቲክሙ ፍሡሐን፤ ለአእዛኒክሙ ሰላም ወለመላትሒክሙ ጽጌ ሮማን፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ አፈዋተ ከርቤ ወልብን፤ ከመ ትባርኩኒ በቡራኬ ኵሉ ጻድቃን፤ ንዑኬ አጋዕዝትየ ኀበ ዝ መካን፡፡

፫. ለዘዚአክሙ ሰላም እብል ለዘዚአክሙ አዕናፍ፤ ለአስናኒክሙ ሰላም ሞገሰ ከናፍር ወአፍ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ብርሃናተ ኵሉ አጽናፍ፤ ይቤለክሙ ሳውል ዜናዊ በውስተ ሐዲስ መጽሐፍ፤ እምግዙር ዕልው ይኄይስ ቈላፍ፡፡

፬. ለልሳንክሙ ወለቃልክሙ ሰላም ለልሳንክሙ ወለቃልክሙ ማሕየዊ፤ ለእስትንፋስክሙ ሰላም ወለጕርኤክሙ ማሕሌታዊ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ዕሥራኤላዊ፤ በዓለ ፍሥሓ አመ ይገብር መርዓዊ፤ አርፍቁኒ አጋዕዝትየ በኪዳን ላዕላዊ፡፡

፭. ለክሣድክሙ ወለመትከፍትክሙ ሰላም ለክሣድክሙ ወለመትከፍትክሙ ሠናይ፤ ለዘባንክሙ ሰላም ወለዕንግድአክሙ ዕንቍ ባሕርይ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ኅሩይ፤ አርፍቁኒ አጋእዝትየ በሕፅንክሙ ልሁይ፤ ከመ ዘረፈቀ አልዓዛር ነዳይ፡፡

## መልክዐ አብርሃም ይሥሐቅ ያዕቆብ በአማርኛ

1. ለዝክረ ስምክሙ፡- ለለዘበ ራሳችሁና ፀጉራችሁ በቍጥር ለስማችሁ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል፤ የዕውቀት ቤት ምሰሶዎች አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! የመከራ ወራት የመሰብሰቢያው ጊዜ ደርሷልና በተለየ አንደበታችሁ ምስጋናዬን ተቀበሉልኝ፡፡

2. ለቀራንብቲክሙ፡- የሮማን አበባ ለሆነ ጒንጫችሁና ለጆሮዋችሁ፤ ለሚያስደስቱ ዐይኖቻችሁና ለቅንድቦቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የልብ ከርቤ መዐዛዎች አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በጻድቃን ኹሉ በረከት ትባርኩኝ ዘንድ ጌቶቼ ሆይ! ወደዚኽ ቦታ ኑ፡፡

3. ለአእናፊክሙ፡- የአፍና የከንፈር ሞገስ ለሆነ ጥርሳችሁና ለአፍንጫችሁ ሰላም እላለሁ፤ የዳርቻ ኹሉ ብርሃኖች አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! መምህር ሳውል በመልእክቱ ውስጥ ‹ከተገዘረ ኀጢአተኛ ቆላፋ ይሻላል› አላችሁ (ይላችኋል)፡፡

4. ለልሳንክሙ፡- ለሚያመሰግን ጒሮሯችሁና ለእስትንፋሳችሁ፤ አዳኝ ለሆነ ቃላችሁና ለአንደበታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ አብርሃም ይሥሐቅና ዕሥራኤላዊ ያዕቆብ ሆይ! ሙሽራ የደስታ በዐልን በሚያደርግ ጊዜ ጌቶቼ ሆይ! በሰማያዊ ቃል ኪዳን አስቀምጡኝ፡፡

5. ለክሣድክሙ፡- የከበረ ዕንቍ ለሆነ ደረታችሁና ለጀርባችሁ፤ ለሚያምር ትከሻችሁና ለአንገታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ አብርሃም ይሥሐቅና የተመረጠ ያዕቆብ ሆይ! ድኻ አልዓዛር በዕቅፋችሁ እንደ ተቀመጠ ጌቶቼ ሆይ! በተቀደሰ ዕቅፋችሁ አስቀምጡኝ፡፡

| | |
|---|---|
| ፮. ለሕፅንክሙ ወለአእዳዊክሙ ሰላም ለሕፅንክሙ ወለአእዳዊክሙ ቅዱሳት፣ ለመዝራዕትክሙ ሰላም ወለዅርናዕክሙ ልዕልት፣ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ዘይት፣ ነቢያት ወሐዋርያት ዘዚኣክሙ አዝርእት፣ እንዘ ክርስቶስ ንጉሥ ወእሙ ንግሥት፡፡ | 6. ለሕፅንክሙ፡- ከፍ ለአለች ክርናችሁና ለመሐል መከንጃችሁ፣ ለተቀደሰ እጆቻችሁና ለጭናችሁ ሰላምታ ይገባል፣ አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! ክርስቶስ ንጉሥና እናቱ ድንግል ማርያም ንግሥት ሲሆኑ ነቢያትና ሐዋርያት የእናንተ ዘሮች ናቸው፡፡ |
| ፯. ለእመትክሙ ወለራኅክሙ ሰላም ለእመትክሙ ወለራሕክሙ ሐዊሳ፣ ለአጻብእክሙ ሰላም ወለአጻብእክሙ ኵልቄ ሠላሳ፣ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ዐምደ ከኒሳ፣ ጸሐፉ መዋዕልየ ምዕተ ወኀምሳ፣ ወለእመ ውህደ ወስኩኒ ስሳ፡፡ | 7. ለእመትክሙ፡- ቍጥሩ ሠላሳ ለሆነ ጣታችሁ፣ ለሚያስደስት ለመሐል እጃችሁና ለክንዳችሁ ሰላምታ ይገባል፣ የምድረ ርስት ምሰሶዎች አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! ዕድሜዬን ከመቶ ኀምሳ አድርጋችሁ ጻፉልኝ፣ ቢጐድልም ስልሳ ጨምሩልኝ፡፡ |
| ፰. ለገቦክሙ ወለከርሥክሙ ሰላም ለገቦክሙ ወለከርሥክሙ ልቡብ፣ ለልብክሙ ሰላም ወለዅልያቲክሙ መዝገብ፣ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ርግብ፣ አሰስሉ ግላ ልብየ በብርሃነ ጽድቁ ለአብ፣ ወበዘሠረቀ እምኔክሙ ዘጽባህ ኮከብ፡ | 8. ለገቦክሙ፡- የጽድቅ መዝገብ ለኾነ ኵላሊታችሁ፣ ለልባችሁና ለተሸፈነ ሆዳችሁ እንዲሁም ለጀርባችሁ ሰላምታ ይገባል፣ አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በአብ የእውነት ብርሃንና ከእናንተ በወጣ የጠዋት ኮከብ ብርሃን የልቤን ጨለማ አርቁልኝ፡፡ |
| ፱. ለኀሊናክሙ ወለአማዑቲክሙ ሰላም ለኀሊናክሙ ወለአማዑቲክሙ ዘነከራ፣ ለነዋየ ውስጥክሙ ሰላም ወለኀንብርትክሙ ዕንቈ ዲቦራ፣ ንዑ ኀቤየ ለአድኅኖ እምነ ኵሉ መከራ፣ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ዘኀየይክሙ ኀበ ምድረ ግብጽ ጊራራ፣ ምስለ እመ ያዕቆብ ርብቃ ወእምሄውት ሣራ፡፡ | 9. ለኀሊናክሙ የዲቦራ ዕንቍ ለሆነ እምብርታችሁና ለሆድ ዕቃችሁ፣ የተለየ ለሆነ አንጀታችሁና ለኅሊናችሁ ሰላምታ ይገባል፣ ከያዕቆብ እናት ከርብቃና ከአያቱ ከሣራ ጋር ወደ ግብጽ ጊራራ ምድር የተሰደዳችሁ አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! ከመከራ ኹሉ ለማዳን ወደ እኔ ኑ፡፡ |
| ፲. ለሐቌክሙ ወለአቍያጺክሙ ሰላም ለሐቍኤክሙ ወለአቍያጺክሙ አዕማድ፣ ለአብራኪክሙ ሰላም ወለአእጋሪክሙ ምዕዋድ፣ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ አሥራወ ኵሉ አንጋድ፣ ዝግቡ ለነ መዝገበ ሣህል ዘኢይከውን ለባዕድ፣ አምጣነ ርቱዕ ይዝግቡ አበው ለውሉድ፡፡ | 10. ለሐቌክሙ፡- ለሚንቀሳቀሱ እግሮቻችሁና ለጕልበቶቻችሁ፣ ለምሶሶዎች ጭኖቻችሁና ለወገባችሁ ሰላምታ ይገባል፣ የነገድ ኹሉ መሠረት አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! አባቶች ለልጆች ማስቀመጥ አግባብ ነውና ሌላ ሳይሆን የይቅርታ ልብን ሰብስቡልን፡፡ |
| ፲፩. ለሰኳንዊክሙ ወለመከየድክሙ ሰላም | 11. ለሰኳንዊክሙ፡- ለማይነቃነቁ ጣቶቻችሁ፣ ስድስት ለሆኑ መረገጫችሁና ለተረከዛችሁ ሰላምታ |

| | |
|---|---|
| ለሰኳንዊክሙ ወለመከየድክሙ ስሱ፤ ለአጻብኢ.ክሙ ሰላም ዘኢ.ይትከወሱ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ለእግዚአብሔር ጽርሐ መቅደሱ፤ ነፍስየ ወሥጋየ በደመ ክርስቶስ ቀድሱ፤ እስመ በኃጥኣት ጽዩዕ ዘሐስሩ ወረኵሱ፡፡ | ይገባል፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በረከሰ ኀጢአት የጐሰቆሉና የረከሱ ነፍሴንና ሥጋዬን በክርስቶስ ደም ቀድሱልኝ፡፡ |
| ፲፪. ለቆምክሙ ሰላም ለቆምክሙ እስከ አርያም ምጡቅ፤ ለአስማቲክሙ ሰላም በምልዐ ዓለም ዕውቅ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ጽጌያተ ብሩር ወወርቅ፤ ይሰወጥ ወስተ ልብየ ሥምረተ ልብክሙ ዛሕቅ፤ ከመ ፍሬ መንፈስ እፍረይ በዐረብ ወሠርቅ፡፡ | 12. ለቆምክሙ፡- በዓለም ኹሉ ለታወቀ ስማችሁና እስከ ሰማይ ለደረሰ ቁመታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የወርቅና የብር ጌጥ አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በፀሐይ መውጫና መግቢያ መንፈሳዊ ፍሬን እንዳፈራ ጥልቅ የልባችሁ ፈቃድ በልቤ ውስጥ ይጨመር፡፡ |
| ፲፫. ለመልክዕክሙ ሰላም ለመልክዕክሙ ዘመልክዐ አዳም አምሳሊ፤ ወለአስማቲክሙ ሥሉስ በስመ ሥላሴ ዘይሄሉ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ብርሃናተ ዓለም ኵሉ፤ እምኀበ አምላክ ማሕየዊ ለወልድክሙ ሰአሉ፤ ከመ ይርከባኒ ምሕረቱ ወሣህሉ፡፡ | 13. ለመልክዕክሙ፡- በሥላሴ ስም ለሚኖር ለሦስት ስማችሁ እና የአዳም መልክ ምሳሌ ለሆነ መልካችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የዓለም ኹሉ ብርሃን አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በቸርነቱና በይቅርታው ይባርከኝ ዘንድ ወደ ልጃችሁ ወደ ማሕየዊ አምላክ ጸልዩልኝ፡፡ |
| ፲፬. ለጸአተ ነፍሳቲክሙ ሰላም ለጸአተ ነፍሳቲክሙ ዘኢ.ያደነግፆን መስቴማ፤ ለበድነ ሥጋክሙ ግንዘት ለመቃብሪክሙ በክፍለ ሰቂማ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ልቡሳነ ዕበይ ወግርማ፤ ለነፍስየ ራሔል ዕብራዊት ምልዕተ ሰቈቃዉ ወጻማ፤ አንግፍዋ በሐሤት ኢ.ትብኪ በራማ፡፡ | 14. ለጸአተ ነፍሳቲክሙ፡- በሰቂማ ክፍል ለመቀበራችሁ፤ ለተገነዘች የሥጋችሁ በድንና ሰይጣን ለአላስደነገጣቸው ለነፍሳችሁ መውጣት ሰላምታ ይገባል፤ ግርማንና ገናንነትን የለበሳችሁ አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በልቅሶና በድካም የዛለች ዕብራዊት ራሔል ነፍሴን በሰማይ እንዳታለቅስ በደስታ አረጋጓት፡፡ |
| ፲፭. እንበለ ምግባር ወገድል ወልድክሙ እንበለ ምግባር ወገድል ወልድክሙ ሐካይ፤ በረድኤትክሙ እርፍቅ ምስለ አልዓዛር ኀሩይ፤ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ካህናተ ብሩህ ሰማይ፤ ሰአሉ ቅድመ ፈጣሪ ሰራዪ ኵሉ ጌጋይ፤ ከመ ያንጽሐኒ በመንፈስ ወማይ፡፡ | 15. እንበለ ምግባር፡- ክፉ ልጃችሁ ያለ ተጋድሎና ያለ በጎ ሥራ ከተመረጠ አልዓዛር ጋር በረድኤታችሁ እንድቀመጥ እርዱኝ፤ የብሩህ ሰማይ አገልጋዮች አብርሃም ይሥሐቅና ያዕቆብ ሆይ! በመንፈስና በውኃ እንዲያነጻኝ በደልን ኹሉ ወደሚያስተሰርይ ፈጣሪ ለምኑልኝ፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለክሙ አብርሃም ምእመን ወይሥሐቅ ቊርባን፤ ወያዕቆብ ኄር ወላዴ ኄራን፤ እምዳሕጸ ኀጢአት ሱቁኒ ለውዱቅ | 16. ሰላም ለክሙ፡- አብርሃም ታማኝ ይሥሐቅ መሥዋዕትና የዕሥራኤላውያን አባት ቸር ያዕቆብ ሆይ! የወደቅሁና የተፍገመገምሁትን እኔን |

| | |
|---|---|
| ወትንቱን፡፡ | በኀጢአት ከመውደቅ ደግፉኝ፡፡ |
| ፲፯. ሰላም ለከ ሰላም ለከ ለፍኖተ ጌጋይ ዘኢተለውኮ፤ በኀዲግ አብ ምስለ ስብኮ፤ አብርሃም በኂሩት ወበአምልኮ፤ እግዚአብሔር አዕበየከ ወባረከከ ባርኮ፤ እስመ ሰመየከ ዲበ ምድር አርኮ፡፡ | 17. ሰላም ለአብርሃም፡- ከጣዖቱ ጋር አባትህን በመተው የበደልን መንገድ ያልተከተልህ በአምልኮት ቸርነት ያለህ አባታችን አብርሃም ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በምድር ላይ ወዳጅ አድርጐሃልና እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገህ፤ መባረክንም ባረከህ፡፡ |
| ፲፰. ሰላም ለይሥሐቅ ሰላም ለይሥሐቅ ዘኢያግዘፈ ክሳዶ፤ ለደኒን ወለተሐርዶ፤ ምስለ አብርሃም በህየ ከመ ይፈጽም ፈቃዶ፤ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ራእይ ወሰዶ፤ ኀበ ንጽሐ ልቡ ነጸረ ወንጹሐ እዶ፡፡ | 18. ሰላም ለይሥሐቅ፡- ለመታረድና ለማዘንበል አንገቱን ለአላደነደነ ለይሥሐቅ ሰላምታ ይገባል፤ ከአብርሃም ጋር በዚያ ፈቃዱን ይፈጽም ዘንድ እግዚአብሔር ወደ ራእይ ተራራ ወሰደው፤ ወደ ልቡ ንጽሕና እና ወደ እጁም ተመለከተ፡፡ |
| ፲፱. ሰላም ለያዕቆብ ሰላም ለያዕቆብ እንተ ወለደ ነገሥተ፤ ወለደብተራ ስምዕ ካህናተ፤ በኀበ ሰዋስወ ርእየ እንዘ ይነውም ሌሊተ፤ ተነበየ ለአሕዛብ መንገለ አሚን ሚጠተ፤ ለሐውልተ ዕብን እመ ቀብዓ ዘይተ፡፡ | 19. ሰላም ለያዕቆብ፡- በምስክሩ ድንኳን የሚያገለግሉ ካህናትንና ነገሥታትን ለወለደ ለያዕቆብ ሰላምታ ይገባል፤ በሌሊት ተኝቶ ሳለ መሰላልን በአየበት ቦታ የድንጋዩን ሐውልት በዘይት ቢቀባ ወደ ሃይማኖት ለመለሳቸው ለአሕዛብ ተናገረ፡፡ |
| ፳. ለዘጸሐፎ በክርታስ ወለዘአጽሐፎ እንዘ ይደርስ፤ ለዘአንበቦ ወለዘተርጐሞ በልሳን ሐዲስ፤ ወለዘሰምዐ ቃሎ በእዝነ መንፈስ፤ በጸሎተ እመ ማርያም ዓራቂተ ኵሉ እምባዕስ፤ ኅቡረ ይምሐረነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ አሜን፡፡ | 20. ለዘጸሐፎ በክርታስ፡- ድርሳናችሁን መልክዐ ጸሎታችን እየደረሰ ያጻፈውን፤ በብራና የጻፈውን፤ ያነበበውን፤ በዐዲስ ቋንቋ የተረጐመውን፤ በእብነ ልቡና ቃሉን የሰማውን ኹሉ ከጥላቻ በምታስታርቅ በእናቱ ማርያም ጸሎት ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድነት ይማረን፤ አሜን፡፡ |
| ኦ አምላከ አበዊነ አብርሃም ይሥሐቅ ወያዕቆብ ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ….. ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ | አቤቱ የቅዱሳን አባቶቻችን የአብርሃም የይሥሐቅ የያዕቆብ አምላክ ሆይ! እኔን ባሪያህን….. ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ፤ ጠብቀኝም፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ |
| አቡነ ዘበሰማያት… | አባታችን ሆይ… |
| ✞ ✞ ✞ | ✞ ✞ ✞ |

## መልክዐ አቡነ አብርሃም (ዘአኀተሞ ገብረ ሥላሴ)

| መልክዐ አቡነ አብርሃም-ግዕዝ | የአባታችን አብርሃም መልክዕ በአማርኛ |
|---|---|
| ፩. ሰላም ለልደትከ አብርሃም ባዕል፤ ዘተሣየጥኮ ፍጹመ በዐውደ ቀዳማይ ቃል፤ ለይሥሐቅ ወልድከ በግዐ ቀራንዮስ ሐቅል፤ እኁዝ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ መስቀል፤ እስመ ዕፀ ሳቤቅ ዘኤዶም ለስርየት ብሂል፡፡ | 1. ለልደትከ፡- በዕፀ ሳቤቅ መስቀል ቀንዶቹ የተያዙ የኤዶም ዕፀ ሳቤቅ ለስርየት ማለት ነውና የቀራንዮ በረሓ በግ ይሥሐቅን በቀዳማዊ ቃል ዐደባባይ ፊጽመህ የተወዳጀኸው ባለ ጸጋ አብርሃም ሆይ! ለመወለድህ ሰላምታ ይገባል፡፡ |
| ፪. አብርሃም አቡየ አብርሃም እኁየ፤ አብርሃም ፍቁርየ፤ ዲበ አትራኖስ ንበር ከመ ትትወከፍ ኪያየ፤ አብርሃም ተወከፍ ውስተ ሕፅንከ ለዘአበሰት ነፍስየ፤ በከመ ሥላሴ ተወከፍከ አብርሃም አቡየ፡፡ | 2. አብርሃም አቡየ፡- አብርሃም አባቴ አብርሃም ወንድሜ አብርሃም ወዳጄ እኔን ትቀበል ዘንድ በአትሮንስ ላይ ተቀመጥ፤ አባቴ አብርሃም ሆይ! ሥላሴን እንደተቀበልህ የበደለች ነፍሴን በእቅፍህ ውስጥ ተቀበልልኝ፡፡ |
| ፫. ሰላም ለዝክረ ስምከ አበ ብዙኃን ዘተብህለ፤ ወለሥዕርትከ ሰላም ዘበምድረ ሥጋ በቈለ፤ ለአዕዋፈ ወንጌል አብርሃም እንተ ኰንኮሙ ምጽላለ፤ ልሳንየ መሬታዊት አመ ታወጽእ ቃለ፤ በሰሌዳ ልብከ አምላካዊ ለይኩን ሥዑለ፡፡ | 3. ለዝክረ ስምከ፡- በሥጋ ምድር ለበቀለ ጠጕርህ እና የብዙዎች አባት ለተባለ ለስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል፤ ለወንጌል ወፎች መጠለያ የሆንኻቸው አባታችን አብርሃም ሆይ! መሬታዊት አንደበቴ ቃልን በአወጣች ጊዜ በአምላካዊ ብራና ልብህ የተጻፈ ይሁን፡፡ |
| ፬. ሰላም ለድማኅከ ከመ ይኩን ትእምርተ፤ እምኍልቄ ዕለታት ሰብዑ ዘወሀበከ ግዝረተ፤ አብርሃም ግዝር ዘኀሊናየ ቍልፈተ፤ ናሁ አብዝኀ ላዕሌየ ወአፈድፈደ ግዝፈተ፤ ወበልደተ ማይ የሐዩ ዘነሥአ ጥምቀተ፡፡ | 4. ለድማኅከ፡- ምልክት ይሆን ዘንድ ከሰባቱ ዕለታት የተነሣ ግዝረትን ሰጠህ፤ አባታችን አብርሃም ሆይ! የልቤን ቆላፋነት ግዘርልኝ፤ እነሆ በላዬ ድንዳኔን ፊጽሞ አብዝቷልና፤ ጥምቀትን የተቀበለም ከውኃ በመወለድ ይድናል፡፡ |
| ፭. ሰላም ለርእስከ ዘአክሊለ ብርሃን አክሊሉ፤ እምጠለ ሱባዔ ገድልከ ዘያበርህ ሥነ ጸዳሉ፤ ዝክረ ጽድቅከ አብርሃም ለትውልደ ትውልድ ይሄሉ፤ ባርከኒ ለወልድከ እስመ ቡራኬ አብ ይደሉ፤ በረከተ ምድር ዘታሕቱ ወሰማይ ዘላዕሉ፡፡ | 5. ለርእስከ፡- ሥነ ጸዳሉ ለሚያበራ መጋደልህ ከሱባኤ ልምላሜ የተነሣ የብርሃን አክሊል አክሊሉ ለሆነ ራስህ ሰላምታ ይገባል፤ የጽድቅህ መታሰቢያ ለልጅ ልጅ የሚኖር አባታችን አብርሃም ሆይ! የአባት በረከት ለልጅ ይገባልና በሰማይና በምድር በረከት ልጅህን ባርከኝ፡፡ |
| ፯. ሰላም ለቀራንብቲከ ነገረ ሃይማኖት እለ ሐተታ፤ ወለአዕይንቲከ ሰላም በግዐ ምሥ | 7. ለቀራንብቲከ፡- የኅልኅታ ምሥጢር በግን ለተመለከቱ ዐይኖችህ እና የሃይማኖትን ነገር |

| | |
|---|---|
| ጢር ዘኅልኅታ፤ አርከ ፈጣሪ አብርሃም ነቢየ ልዑል ዘበበፆታ፤ ሀበነ ለደቂቅከ ውስተ ሰማያዊት ኤፍራታ፤ ዘጥቅማ ነዊህ ወዓቢይ አረፍታ፡፡ | ለመረመሩ ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል፤ በየወገኑ የልዑል ነቢይና የፈጣሪ ወዳጅ አብርሃም ሆይ! ቅጥሯ የረዘመ ግድግዳዋ ታላቅ የሆነ ቤትን በሰማያዊት ኤፍራታ ውስጥ ለልጆችህ ስጠን፡፡ |
| ፰. ሰላም ለአእዛኒከ መሳክወ ንባብ እለ ተብህላ፤ ወለመላትሒከ ሰላም እለ ተሠርገዋ ሥነ ዕብላ፤ አብርሃም ጸሐፍ በብርዐ ክርስቶስ ርእሰ መሐላ፤ ፊደላተ በበሰብኦሙ ለዘይመጽእ ከዋላ፤ ከመ ይክፍለነ በሣህሉ ምድረ ጽድቅ ወተድላ፡፡ | 8. ለአእዛኒከ፡- የጨረቃን ደም ግባት ለተዋበ ጉንጭህ እና የቃል መስኮት ለተባሉ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አብርሃም ሆይ! በይቅርታው የደስታንና የጽድቅን ምድር ያድለን ዘንድ የቃል ኪዳን ራስ በሆነ በክርስቶስ መጻፊያ በኋላ የሚመጡት ሰዎችን ስማቸውን ጻፍ፡፡ |
| ፱. ሰላም ለአእናፊከ አፈዋተ ወንጌል ዘአጼነዋ፤ ወለከናፍሪከ ጽጌ ዘማዕፆ ትዕግሥት አጸዋ፤ አዕጋረ ልብከ አብርሃም በፍኖተ አሚን እለ ተለዋ፤ ለወልድከ እምባሕረ ጌጋይ አዕድወኒ ነዋ፤ ከመ ለዮርዳኖስ ቅድመ ኢያሱ አደዋ፡፡ | 9. ለአእናፊከ፡- የትዕግሥት መዝጊያ ለዘጉት ለአበባ ከንፈርህ እና የወንጌል ሽቱን ለአሸተቱ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ የልብህ እግሮች የሃይማኖት ጐዳናን የተከተሉ አብርሃም ሆይ! ኢያሱ አስቀድሞ ዮርዳኖስን እንደተሻገረ እነሆ ልጅህን የበደልን ባሕር አሻገረኝ፡፡ |
| ፲. ሰላም ለአፉከ አንቀጸ ንባብ ወቃል፤ ወለአስናኒከ ሰላም ዘኀበሪሆን ጽዱል፤ ፈለገ አዕምሮ አብርሃም ጽጌ ገዳማት ዘኮል፤ ኅሩይ በተአምኖ ለኪዳነ አምላክ ልዑል፤ እስመ ለጻድቅ ኀይለ ጸሎቱ ታሠልጥ ወትብል፡፡ | 10. ለአፉከ፡- መልካቸው ለሚያበራ ጥርሶችህ እና ለንባብና ለቃል በር ለሆነ አፍህ ሰላምታ ይገባል፤ የጻድቅ ሰው የጸሎቱ ኀይለ ግዳጅ ትፈጽማለችና የዕውቀት ምንጭ የበረሓ እንኮይ አበባ አብርሃም ሆይ! ለልዑል አምላክ ቃል ኪዳን በመታመን ተመረጥህ፡፡ |
| ፲፩. ሰላም ለልሳንከ ዘነበበ ጽድቀ ወአምልኮ፤ ወለቃልከ ክቡር ለይሥሐቅ እንተ ባረኮ፤ በፍኖተ አሚን አብርሃም ለእግዚአብሔር ጊዜ ተለውኮ፤ እምሀገረ ዕልወት ከላውዴ ዎን አመ ተኀድግ ስብኮ፤ ከመ ጽላሎት ወህልም ለዓለም ረሰይኮ፡፡ | 11. ለልሳንከ፡- ይሥሐቅን ለባረከ ለከበረ ቃልህና አምልኮትንና ጽድቅን ለተናገረ አንደበትህ ሰላምታ ይገባል፤ አቡነ አብርሃም ሆይ! በሃይማኖት ጐዳና እግዚአብሔርን በተከተልኸው ጊዜ ከክሕደት ሀገር ከላውዴዎን ጣዖትን በምትተው ጊዜ ዓለምን እንደ ጥላና ሕልም አደረግኸው፡፡ |
| ፲፪. ሰላም ዕብል ለእስትንፋስከ አበሜ፤ ወለጕርዔከ ኤፌሶን ስቴ በረከት ወከራሜ፤ መዐዛ ቅዱሳን አብርሃም ጽጌ ፊካትም ወልምላሜ፤ ኑኀ ዘመንየ ከመ ይረክብ ፍጻሜ፤ በጸሎትከ አባ ወስከኒ ዕድሜ፡፡ | 12. ለእስትንፋስከ፡- የበረከትና የወይን መገኛ ለሆነ ለኤፌሶን ጉሮሮህ እና ለሽቱ እስትንፋስህ ሰላም እላለሁ፤ የቅዱሳን መዐዛ የልምላሜና የወንዝ ዳር አበባ አብርሃም ሆይ! የዘመኔ ርዝመት መጨረሻን ያገኝ ዘንድ አባት ሆይ! በጸሎትህ ዕድሜን ጨምርልኝ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፲፫. ሰላም ለክሣድከ ሃይማኖተ ሥሉስ ዘአጥብአከ፥ በኊረ ሰማዕታት ይሥሐቅ አመ በምሥዋዕ ሰከብከ፥ ወረደ መልአክ ሰማያዊ ከመ ይቤዙ ነፍሰከ፥ እለ ርእዩ ቤተ አብርሃም ወቤተ ሣራ እምከ፥ ሰማዕታት ከዐዉ ደሞሙ ምስሌከ፡፡ | 13. ለክሣድከ፡- የሰማዕታት አለቃ አባታችን ይሥሐቅ ሆይ! በመሠዊያው በተኛህ ጊዜ የሥላሴ ሃይማኖት ለአስጨከነህ አንገትህ ሰላምታ ይገባል፥ ነፍስህን ያድን ዘንድ ሰማያዊ መልአክ ወረደ፥ የአባትህ የአብርሃምንና የእናትህን የሣራን ቤት የተመለከቱ ሰማዕታት ከአንተ ጋር ደማቸውን አፈሰሱ፡፡ |
| ፲፬. ሰላም ለመትከፍትከ እምአርዑተ ጌጋይ ዘተግኅሠ በተውሳከ አሚን ገራህተ ቃለ ተዋህዶ ሐረሰ፥ በዓለ ገራህት አብርሃም እንተ ረከብከ ሞገሰ፥ ከመ ታድኅነኒ አስተበቍዓከ አንሰ፥ እምነ ጸላዒ ውስተ ከርሡ ዐመፃ ዘጸንሰ፡፡ | 14. ለመትከፍትከ፡- ሃይማኖት ማሳን ለመጨመር በተዋሕዶ ቃል ለራሰ ከበደል ቀንበር ለተወገደ ትከሻህ ሰላምታ ይገባል፥ ባለሟልነትን የአገኘህ ባለ ማሳ አብርሃም ሆይ! ከባሕርይው ዐመፃን ከጸነሰ ጠላት ታድነኝ ዘንድ እማልድሃለሁ፡፡ |
| ፲፭. ሰላም ለዘባንከ ሕገ አምላኩ ዘተሞጥሐ፥ ወለእንግድዓከ ሰላም መዝገበ ሃይማኖት ወአምኅነ፥ ኅሩይ አብርሃም እፀንሐከ ጸኒሐ፥ ሀበኒ ብዕለ ጽድቅከ ሠርከ ወነግሀ፥ እስመ ዘእንበሌከ ኢይረክብ ሰላመ ወፍትሐ፡፡ | 15. ለዘባንከ፡- የሃይማኖትና የእጅ መንሻ ግምጃ ቤት ለሆነ ደረትህ እና የአምላኩን ሕግ ለተጐናጸፈ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል፥ የተመረጥህ አባታችን አብርሃም ሆይ! ደጅ መጥናትን ደጅ እጠናሃለሁ፥ ያለ አንተ ሰላምንና እውነትን አላገኝምና ከጽድቅህ በረከት በጠዋትና በማታ ስጠኝ፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለሕፅንከ ህየንተ ጽድቁ ወኂሩቱ፥ ለእግዚአብሔር አምላክ ወበእንተ ድንግል ወላዲቱ፥ በአስተብቍዖ ይብሉከ ካህናት ለለዕለቱ፥ ውስተ ሕፅነ አብርሃም አበ ኵልነ ወሕፅነ ደቂቁ ክልኤቱ፥ አዕርፍ ነፍሶሙ ለአበው ዘሞቱ፡፡ | 16. ለሕፅንከ፡- ስለ እናቱ ድንግልና ስለ አምላክ እግዚአብሔር ጽድቁና ቸርነቱ ለሆነ እቅፍህ ሰላምታ ይገባል፥ ካህናት በየቀኑ ‹በመወለድ ወደ ኹላችን አባት ወደ አብርሃምና ወደ ኹለቱ ልጆቹ እቅፍህ የሞቱ አባቶችን ነፍስ አሳርፍ› እያሉ ይማልዱሃል፡፡ |
| ፲፯. ሰላም ዕብል ለአእዳዊከ ክልኤ፥ እለ ኢሐነጻ ህቀ ማኅፈደ ዕልዋን ወዝንጋዔ፥ መርዓዌ ምግባር አብርሃም ወሃይማኖት ጉባኤ፥ አብሃኒ እምከብካብከ እንዘ ትጼውዕ ጽዋዔ፥ ልበ ምውታን ድኅረ ይትገበር ትንሣኤ፡፡ | 17. ለአእዳዊከ፡- የሰነፎችን ማደሪያና መዘንጋትን በጥቂቱ ለአልሠሩ ለኹለት እጆችህ ሰላም እላለሁ፥ የጉባኤ ሃይማኖትና የበጐ ሥራ ሙሽራ አባታችን አብርሃም ሆይ! በኋላ ትንሣኤ ሙታን በሚደረግ ጊዜ እኔን ልጅህን መጥራትን ጠርተህ ከሠርግህ እድምተኛ አድርገኝ፡፡ |
| ፲፰. ሰላም ለመዛርዒከ እማዕተበ ጌጋይ ዘተፈልጠ፥ ወለኵርናዕከ ሰላም አቅርንተ አምልኮ ቀጥቀጠ፥ ኰኵሐ ሃይማኖት አብርሃም ዘበትረ ትንሣኤ ፀበጠ፥ በስምከ | 18. ለመዛርዒከ፡- የጣዖትን ቀንዶች ለቀጠቀጠ ክርንህ እና ከኀጢአት ማዕተብ ለተለየ መከንጃህ ሰላምታ ይገባል፥ የትንሣኤ በትርን የጨበጠ የሃይማኖት መሠረት አብርሃም ሆይ! በስምህ |

| | |
|---|---|
| ለዘሰአሉ ወአ ስተብቍዑ ኀዳጠ፤ እግዚአብሔር አምላክ ዜዋ ጽዮን ሜጠ፡፡ | ለለመኑና በጥቂቱም ለማለዱ እግዚአብሔር አምላክ የጽዮንን ምርኮ መለሰ፡፡ |
| ፲፱. ሰላም ለእመታቲከ አረፍተ ሃይማኖት እለ ወጠኑ፤ ወለእራኅከ ስፉሕ ለውሂበ ምጽዋት በበዘመኑ፤ አብርሃም ኅሩይ ለእግዚአብሔር ምእመኑ፤ በእግረ አምልኮ እለ ኪያከ ዴገኑ፤ ንዋየ ኀላፊ ዓለም ዘበምድር መነኑ፡፡ | 19. ለእመታቲከ፡- በየዘመኑ ምጽዋትን ለመስጠት ለተዘረጋ መሐል እጅህ እና የሃይማኖት ግድግዳን ለጀመሩ ክንዶችህ ሰላምታ ይገባል፤ የእግዚአብሔር ታማኝ የተመረጥህ አብርሃም ሆይ! በአምልኮ እግር አንተን የተከተሉ በምድር ያሉ የሚያልፍ ዓለም ገንዘብን ናቁ፡፡ |
| ፳. ሰላም ለአጻብዒከ በሀሳበ የውጣ ዘተኈለቁ፤ ወለአጽፋሪከ ጽዕድዋን እምግብራተ ጌጋይ ዘርኅቁ፤ ብእሲ ሰላም አብርሃም ለእግዚአብሔር ደቂቁ፤ ደቂቅከ በሃይማኖት ውስተ ሐፅንከ ይርፍቁ፤ ቅድመ ገጸ አምላክ እግዚእከ አስተምሕር በህቁ፡፡ | 20. ለአጻብዒከ፡- ከክፉ ሥራ ለራቁ ለነጡ ጥፍሮችህ እና በዐሥር ቍጥር ለተቈጠሩ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ የሰላም ሰው የእግዚአብሔር ልጅ አብርሃም ሆይ! ልጆችህ በሃይማኖት እቅፍህ ውስጥ ይቀመጡ ዘንድ በጌታህ አምላክ ፊት አማልድ፡፡ |
| ፳፪. ሰላም ለልብከ ምስለ ኵልያቲከ ዘኀለየ፤ ሃይማኖተ ሥሉስ ቅዱስ ወምግባረ ጽድቅ ጽጉየ፤ ለነዌ ወልድከ አብርሃም አቡየ፤ እምባሕረ እሳት ከመ ያቁርረኒ ማየ፤ ለገብርከ አልዓዛር ፈንዎ ኀቤየ፡፡ | 22. ለልብከ፡- በሥላሴ ማመንና የአማረ በጐ ሥራን ከኵላሊትህ ጋር ለአሰበ ልብህ ሰላምታ ይገባል፤ አባቴ አብርሃም ሆይ! ለልጅህ ነዌ ከእሳት ባሕር በውኃ ያቀዘቅዘኝ ዘንድ ባሪያህ አልዓዛርን ወደ እኔ ላክልኝ፡፡ |
| ፳፫. ሰላም ለኀሊናከ ዘኀሊና አምላክ ፈጠሮ፤ ወለአማዑቲከ ሰላም ለማየ ኀጢአት ዘኢያግመሮ፤ አብርሃም ሥርግው በጽጌ ሃይማኖት ወተፋቅሮ፤ ሠውረኒ እምገጸ ሞት ከመ ለሂኖክ ሠወሮ፤ እግዚአብሔር አምላክ ቀዳሚ አዕሚሮ፡፡ | 23. ለኀሊናከ፡- የኀጢአት ውኃን ለአልተሸከመ አንጀትህ እና የአምላክ ኅሳብ ለፈጠረው ኅሊናህ ሰላምታ ይገባል፤ በሃይማኖትና በፍቅር የተዋብህ አባታችን አብርሃም ሆይ! አስቀድሞ አውቆ እግዚአብሔር አምላክ ሄኖክን እንደሠወረው ከሞት ፊት ሠውረኝ፡፡ |
| ፳፬. ሰላም ለንዋየ ውስጥከ በተሠግዎ ቃል እንተ ይሄሉ፤ ወለኀንብርትከ ቀላይ ለኢያሪኮ በማዕከሉ፤ ብፁዕ አብርሃም መሠረተ አሚን በኀበ ኵሉ፤ በሎሙ ለአፅራርየ እምዐጸደ ተስናን ሰስሉ፤ ወለነቢያት ይብሎሙ ነፍሰ ፀር ቅትሉ፡፡ | 24. ለንዋየ ውስጥከ፡- በኢያሪኮ መካከል ለአለ እምብርትህ ምንጭ እና በቃል ሰው መሆን ለሚኖር ሆድ ዕቃህ ሰላምታ ይገባል፤ በኹሉ ዘንድ የሃይማኖት መሠረት የሆንህ ብፁዕ አባታችን አብርሃም ሆይ! ጠላቶቼን ‹ከጥላቻ ብቻ ወግዱ› በላቸው፤ ነቢያትም ‹የጠላትን ነፍስ አጥፉ› ይበሏቸው፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፳፭. ሰላም ለሐቌከ ዘቀነተ ጽድቀ ከመ አእኑግ፤ ወለአቀኍያጺከ አብላቅ አዕማደ ሥርዐት ወሕግ፤ ምክሐ ራትዓን አብርሃም ወጽንዓ ኅሩያን አዕሩግ፤ ሀበኒ ኀይለ እጽብኦሙ ወእማኦሙ በደርግ፤ ለሰይጣን ሲኦል ወለሞት ጸዋግ፡፡ | 25. ለሐቌከ፡- የሥርዐትና የሕግ ምሰሶዎች ለሆኑ የጭኖችህ ምሰሶዎች እና እንደ ጌቶች ጽድቅን ለታጠቀ ወገብህ ሰላምታ ይገባል፤ የተመረጡ ሽማግሌዎች ጽናትና የቅኖች መመኪያ አብርሃም ሆይ! ሰይጣንን፣ ሲኦልንና ክፉ ሞትን በአንድነት ፈጽሜ አሸንፋቸው ዘንድ ብርታትን ስጠኝ፡፡ |
| ፳፮. ሰላም ለአብራኪከ አድያመ ሃይማኖት ዘየዱ፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ፤ ቈላተ ሠርዌ ወኀኵል አመ በጼዋዌ ወረዱ፤ ዕሥራኤል ሰአሉ እንዘ ይብሉ ለእግዚአብሔር በዐውዱ፤ ኪዳነ አብርሃም ተዘከር ምስለ ይሥሐቅ ወልዱ፡፡ | 26. ለአብራኪከ፡- አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሃይማኖትን አውራጃ ለዞሩ ጕልበቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ ወደ ጥፋትና መከራ ቆላ ዕሥራኤል በምርኮ በወረዱ ጊዜ በእግዚአብሔር ዐደባባይ ‹ከልጁ ይሥሐቅ ጋር የአብርሃምን ቃል ኪዳን አስብ› እያሉ ለመኑ፡፡ |
| ፳፰. ሰላም ለሰኳንዊከ ምስለ መከየድከ እለ ረትዑ፤ በተውሳከ አሚን ይሑሩ ወአሣዕነ ጽድቅ ይቅፅዑ፤ ምስለ ሐዋርያ አብርሃም ኅበ ርስቶሙ ይባዑ፤ በብካይ ወላህ ሶበ ስመከ ጸውዑ፤ እምአዘቅተ ቅኔ መሪር ዕሥራኤል ወጽኡ፡፡ | 28. ለሰኳንዊከ፡- ሃይማኖትን በመጨመር ይሔዱ ዘንድ የጽድቅንም ጫማ ይጫሙ ዘንድ ከመረገጫ ጋር ለቀኑ ተረከዞችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከሐዋርያ አብርሃም ጋር ወደ ርስታቸው ይገቡ ዘንድ በመሪር ልቅሶ ስምህን በጠሩ ጊዜ ከመራር ባርነት ጉድጓድ ዕሥራኤል ወጡ፡፡ |
| ፳፱. ሰላም ለአጻብዒከ እለ ትኩላን በበገጹ፤ ወለአጽፋሪከ ጽዕድዋን ዘእምኔሆን ሠረፁ፤ ኆኅተ ሃይማኖት አብርሃም ወለቤተ ምግባር አንቀጹ፤ የሐውጻኒ እግረ ጽድቅከ ለድምፀ ቃለ ቀርን ድምፁ፤ በከመ ሥላሴ ኪያከ እምሰማይ ሐወፁ፡፡ | 29. ለአጻብዒከ፡- ከእነርሱ ለበቀሉ ለነጡ ጥፍሮችህ እና በየፊቱ ለበቀሉ (ለተተከሉ) ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ የሃይማኖትና የበጐ ምግባር በር አብርሃም ሆይ! ሥላሴ አንተን ከሰማይ እንደጐበኙ የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ የሆነ የጽድቅህ እግር ይጐብኘኝ፡፡ |
| ፴. ሰላም ለቆምከ ሜላተ ሃይማኖት ዘተከድነ፤ ወለመልክዕከ ሰላም ዘተሠርገወ ብርሃነ፤ ተወካፌ ነግድ አብርሃም ዘረሰይኩከ ፀወነ፤ በአእጋረ ሞት ሶበ በጻሕኩ ፍጡነ፤ በቃለ ብሥራት በለኒ ሀለውኩከ አነ፡፡ | 30. ለቆምከ፡- ብርሃንን ለተሸለመ መልክህ እና የሃይማኖት ሐርን ለለበሰ ቁመትህ ሰላምታ ይገባል፤ መጠጊያ ያደረግሁህ እንግዳን የምትቀበል አባታችን አብርሃም ሆይ! በሞት እግር ፈጥኜ በደረስሁ ጊዜ በምሥራች ቃል ‹እኔ አለሁልህ› በለኝ፡፡ |
| ፴፩. ሰላም ለጸአተ ነፍስከ እምዐጸደ ሥጋ ማሳኒ፤ ወለበድነ ሥጋከ እምወርቅ ወእምብሩር ዘይሜኒ፤ አብርሃም አቡየ ለወልደ ዚኣከ ተአማኒ፤ ከመ እዜኑ ለስምከ ወለክብርከ | 31. ለጸአተ ነፍስከ፡- ከወርቅና ከብር ይልቅ ለሚያምር ለሥጋህ በድን እና ከሚጠፋ የዐጸደ ሥጋ ለነፍስህ መውጣት ሰላምታ ይገባል፤ አባቴ አብርሃም ሆይ! ስምህን አስተምርና ክብርህን አመሰግን ዘንድ ታማኝ ልጅህን ባርከኝ፤ ተስፋም ሁነኝ፡፡ |

እገኒ፤ ባርከኒ ለወልድከ ወተስፋ ኩነኒ፡፡

፴፪. ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ በእደ ይሥሐቅ ጻድቅ፤ ወለመቃብሪከ ቅሩጽ ዘተሣየጥኮ በሠርቅ፤ ምዕላደ ምግባር አብርሃም ወዘሃይማኖት ንድቅ፤ አስተምሕር በእንቲኣየ ቅድመ ክርስቶስ ሊቅ፤ ከመ ይኩን ፍኖትየ ፍኖተ ዘጽድቅ፡፡

፴፫. ሰላም ለፀአትከ እምሀገረ ስሕተት ወፍዳ፤ ለብፅአትየ ዓዲ ኀበ ምድረ ርስት ጽጌ ረዳ፤ አብርሃም ትኩል ለገነተ አሚን ውስተ ዐጸዳ፤ ተወከፍ ወትረ ጸሎትየ ዘአቅረብኩ ጋዳ፤ በእንተ ማርያም ድንግል ወፍቁር ወልዳ፡፡

፴፭. ናሁ አቅረብኩ ለስምከ አምኀ ስብሐት ዘኢይበሊ፤ እግዚአብሔር አምላክ በኀይለ ሥልጣኑ ከሀሊ፤ በእንቲኣየ አብርሃም ኀበ ክርስቶስ ጸሊ፤ ወእምየ ሣራ ኀበ ወላዲቱ ሰአሊ፤ ከመ ይዕቀበኒ በመስቀሉ እምሰይጣን ማኅጎሊ፡፡

ኦ አምላከ አቡነ አብርሃም ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ..... ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቡነ ዘበሰማያት…

✞ ✞ ✞

32. ለግንዘተ ሥጋከ፡- በወርቅ በገዛኸው በተቀረጸ መቃብር ለመቀበርህ እና በጻድቅ ይሥሐቅ እጅ ለሥጋህ መገነዝ ሰላምታ ይገባል፤ የሃይማኖት አዳራሽና የምግባር አልፍኝ አብርሃም ሆይ! መንገዴ የእውነት መንገድ ይሆን ዘንድ ከአምላክ ክርስቶስ ፊት ስለ እኔ አማልድ፡፡

33. ለፀአትከ፡- ዳግመኛ ከስሕተትና ከፍዳ ምድር ለመውጣትህ ሰላምታ ይገባል፤ በሃይማኖት የተክል ቦታ ውስጥ የተተከልህ አባታችን አብርሃም ሆይ! የአቀረብኩትን የእጅ መንሻ ስለ ድንግል ማርያምና ስለ ተወደደው ልጇ ጸሎቴን ሁልጊዜ ተቀበልልኝ፡፡

35. ናሁ አቅረብኩ፡- ኹሉን በሚችል በእግዚአብሔር አምላክ ኀይል የማያረጅ የምስጋና እጅ መንሻን እነሆ ለስምህ አቀረብሁ፤ አባቴ አብርሃም ሆይ! በመስቀሉ ከአጥፊ ጠላት እንዲጠብቀኝ ስለ እኔ ወደ ክርስቶስ ጸልይልኝ፤ እናቴ ሣራም ወደ እናቱ ለምኚልኝ፡፡

አቤቱ የአባታችን አብርሃም አምላክ ሆይ! እኔን ባሪያህን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ፤ ጠብቀኝም፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አባታችን ሆይ…

✞ ✞ ✞